## የኤጀንሲው ስም፡ የሕዝብ ምክር ቤት ቢሮ (Office of the People's Counsel)

## ተልዕኮ፡

የሕዝብ ምክር ቤት ቢሮ በኮሎምቢያ ግዛት ዲስትሪክትት ገለልተኛ ኤጀንሲ ነው። ቢሮው በከንቲባው በተሰየመ የሕዝብ ምክር ቤት የሚመራ ነው። በህግ፤ የOPC (የሕዝብ ምክር ቤት ቢሮ ማለት ነው) የህግ ቡድን እና የሸማቾች ተወካዮች በግዛቱ ውስጥ ላሉ የተፈጥሮ ጋዝ፣ የኤሌትሪክ እና የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ይሟገታሉ። የኮሎምቢያ ግዛት ህግ OPCን በኮሎምቢያ ግዛት የሕዝብ አገልግሎቶች ኮሚሽን ፊት እንድ የሁሉም አገልግሎት ነክ ጉዳዮች ተወካይ (በእንግሊዝኛው ምጻረ ቃል PSC) አድርጎ ሾሞታል። OPC በተጨማሪም የኮሎምቢያ ግዛት የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ፍላጎት በፍርድ ቤቶችና በፌዴራል ተቆጣጣሪ ኮሚሽኖች ፊት ይወክላል።

OPC ጥራት ላለው የፍጆታ አገልግሎት እና ለሚዛናዊ መስተንግዶ ተመጣጣኝ ለሆነ፣ ፍትሃዊ እና ከመድልዎ ለጸዱ አገልግሎቶች ይሟገታል። ከፍጆታ አቅራቢ ኩባንያዎች ጋር በክፍያ ወይም በአገልግሎት ዙሪያ ላይ በሚነሱ ሙግቶች ግለሰብ ተጠቃሚዎችን ያግዛል። እና የቴክኒክ እገዛ እና የተጠቃሚ ትምህርትን ለማህበረሰብ ተሟጋቾች፣ ለጉርብትና አካባቢ አማካሪ ኮሚሽኖች ለሲቪክ እና ዜጋ ማህበራት እና ለሌሎች የማህበረሰብ ቡድኖች ያቀርባል።

## ዋና ዋና መርሃ ግብሮችና አገልግሎቶች፡

**የተጠቃሚ ቅሬታዎች፡** የፍጆታ ሒሳብዎ ወይም አገልግሎቱ ላይ ችግር ካለዎት OPC ሊረዳዎት ይችላል። የOPC ሰራተኞች በእርስዎ ቦታ የፍጆታ ኩባንያውን ስለ ችግሩ መደበኛ ባልሆነ መልኩ ሊያናግርልዎት ይችላል። ቅሬታዎን መደበኛ ባለሆነ መልኩ መፍታት ካልተቻለ OPC ከPSC ፊት የሚወክልዎት ጠበቃ ሊያቀርብልዎት ይችላል።

**የማህበረሰብ ተደራሽነት፡** OPC የቁጥጥሩ ሂደት ውስጥ ሕዝባዊ ተሳትፎን ያበረታታል። በተጨማሪም ለኮሎምቢያ ግዛት ተጠቃሚዎች የጠቅላላ መረጃ እና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል። የOPC ሰራተኞች የኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ ለሚደረጉ ANC፣ የሲቪክ ማህበራትና ሌሎች የማህበረሰብ ስብሰባዎች ላይ ህብረተሰቡን ስለ ወቅታዊ የፍጆታ ጉዳዮች እና ተለምዶዎች ለማስተማር ንግግር ያደርጋሉ። በተጨማሪም OPC ለዲሲ ህብረተሰብ ተሟጋቾች እና የዜጎች አደረጃጀቶች እንደ የቴክኒክ ምንጭነት ያገለግላሉ። አንድ የስራ ባልደረባችን በቅርቡ የሚደረግ የማህበረሰብ፣ የሲቪክ፣ የተከራይ ወይም ANC ስብሰባዎች ላይ ስለ ፍጆታ ጉዳይ ንግግር እንዲያደርግ ለመጠየቅ የOPCን የተጠቃሚዎች አገልግሎት ክፍል (CSD) ያግኙ። እባክዎን OPCን ከስብሰባው ቀን ሁለት ሳምንት አስቀድመው ያነጋግሩ።

**ህትመቶች፡** OPC ህብረተሰቡን ስለ ፍጆታ ጉዳዮች፣ የተጠቃሚ ጥብቅና እንቅስቃሴዎች እና በሂደት ላይ ስላሉ ክርክሮች የደረሱበትን ደረጃ ለማሳወቅ ፋክት ሺቶች፣ ብሮሹሮች፣ በራሪ ወረቀቶች እና ሌሎች ጽሁፎችን ያሳትማል። የOPC የትምህርትና የተደራሽነት ጥረቶች በተሻለ መልኩ በድህረ ገጹ [www.opc-dc.gov](http://www.opc-dc.gov) ላይ እና በFacebook ገጹ ላይ በሚያቀርበው መረጃ ይበልጥ ይጎላሉ። OPC. በተጨማሪም በተጠቃሚ ማስጠንቀቂያዎች፣ በጋዜጣ ጽሁፎች፣ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ዝግጅቶች እና የግዛት አስተዳደሩ ንብረት በሆኑ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ላይ በሚተላለፉ የህብረተሰብ አገልግሎት ማስታወቂያዎች ህብረተሰቡ በእንቅስቃሴዎቹ ላይ ያለውን ንቃተ ህሊና ይጠብቃል።

## ዋና ክፍሎች፡

**ዳይሬሬክተቶሬሬት**: የሕዝብ አማካሪ ሳንድራ ማታቨስ-ፍራይ የኤጀንሲውን የዕለት ተዕለት እንቅስቀቃሴ ይመራሉ፣ የዓመት በጀቱን ያቅዱና ያስተዳድራሉ፣ ኤጀንሲውን በኮሎምቢያ ግዛት ኮሚቴ PSC እና የተወካየዮች ምክር ቤት ይወክላሉ እና በኤጀንሲው ተልዕኮ መሰረት ፖሊሲዎችን ያዘጋጁና ስራ ላይ ያውላሉ።

**የተጠቃሚ አገልግሎቶች**: ይህ ክፍል የፍጆታ ተጠቃሚዎችን ስለ ፍጆታ አገልግሎት የተመለከቱ መብቶቻቸውን ለማስተማር ሥር ሰደድ የተደራሽነት መርሃግብሮችን ያካሀሂዳል። እና የደረጃ አወጣጥ ሂደት ላይ ለተጠቃሚው ተሳትፎ ድጋፍ ያቀርባል።በተጨማሪም CSD የተጠቃሚ ቅሬታዎችን እና ጥያቄዎችን ያስተናግዳል፣ ለተለያዩ የፍጆታ ተጠቃሚ ቡድኖች እና የማህበረሰብ ፎረም ተሳታፊዎች የቴክኒክ ድጋፍ ያቀርባል።

**የህግ ስርዓት አገልግሎቶች**: ይህ ክፍል በPSC፣ በፌዴራል ተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች፣ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች እና በኮሎምቢያ ግዛት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ፊት የፍጆታ ኩባንያዎችን በተመለከተ ጉዳይ ለኮሎምቢያ ግዛት ተጠቃሚዎች ይሟገታል። ይህ ቀጣይ የክርክር ሂደቶችን አጠቃላይ የስትራቴጂ ዝግጅት እና የክርክር ቡድኖችን፣ ሰራተኞችን፣ ከፍተኛ አማካሪዎችን የባለሙያ ምስክሮችን አመራር ያጠቃልላል።

**የማብራራት አገልግሎቶች**: ስለ ዲ.ሲ. የሕዝብ ምክር ቤት ቢሮ ጥያቄዎች ካለዎት ቢሮአችን በ(202)727-3071 ደውለው ሊያገኙን ይችላሉ። በሚደውሉ ወይም ቢሮአችንን በሚጎበኙ ጊዜ እንረዳዎት ዘንድ የስራ ባልደረባ የሆነ ሰው በቀጥታ ከአስተርጓሚ ጋር ያገናኞታል።

**አድራሻ፡**

**Office of the People's Counsel**
**District of Columbia**
**1133 15th Street, NW, Suite 500**
**Washington, DC  20005**